የገቢዎች ሚኒስቴር
Ministry of Revenues

# ገቢዎችን ህልውናችን

14ኛ ዓመት | ቁጥር 169 | ጥር 2016 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል



## በውስጥ ገፃችን



ለዘመነ የግብር አሰባሰብ
ገጽ 3



አስሩ የፔሌ ልዩ መታወቂያዎች
ገጽ 5


### ገቢዎችን የተመለከቱ ወቅታዊ፣ ትኩስ እና የተሟሉ መረጃዎችን ለማግኘት፡- በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎቻችን ይጎብኙ

1. በድረ ገጽ፦ www.mor.gov.e
2. በቴሌግራም፦ https://t.me/MoREthiopiaOfficial/169
3. በፌስቡክ፡- https://www.facebook.com/ERCA.info or ministryofrevenuesofethiopia /የገቢዎች ሚኒስቴር/
4. በዩትዩብ፦ https://www.youtube.com/@ministryofrevenuesofethiop1677/videos Or ministryofrevenuesofethiopia
5. በቲክቶክ አጫጭር መረጃ https://vm.tiktok.com/ZM61hdty2/

### በቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን

6. ዋልታ ቴሌቪዥን ሰኞ ማታ ከ 2፡30 ጀምሮ
7. ፋና ቴሌቪዥን ሐሙስ ማታ ከ2፡00 ዜና በኋላ
8. ኢቲዮጵያ ቴሌቪዥን /ኢ.ቢ.ሲ/ ቅዳሜ ማታ ከ2፡00 ዜና በኋላ

### በሬድዮ ፕሮግራሞቻችን

9. ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ 98.1 ሐሙስ ማታ ከ2፡30 ጀምሮ
10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬድዮ 93.1 ማክሰኞ ጠዋት ከ2፡30 ጀምሮ
11. በወርሃዊ ጋዜጣችን፡- ገቢያችን ህልውናችን

# የማያስጥል ዝነኝነት

**ካለፈው የቀጠለ**



ሰዎች በተለያዩ መስኮች ታዋቂነትን ቢያተርፉም በሕግ ፊት እኩል ናቸውና ሕግን ሲተላለፉ ከመጠየቅ እና ከመቀጣት አያመልጡም። ከዚህ አኳያ ባለፈው ዕትማችን የተወሰኑትን የዓለማችን እውቅ ሰዎች በታክስ ወንጀል ላይ ተሳትፎ እና ቅጣት አስነብባችሁ ነበረና ቀጣዮቹን እነሆ።

**ማርክ አንቶኒ፡-** የሙዚቃ ሰዉ ማርክ አንቶኒ የታዋቂዋ ሙዚቃ አቀንቃኝ ጀኒፈር ሎፔዝ ባል ሲሆን እ.ኤ.አ ከ2000 እስከ 2004 ካገኘው 15.5 ሚልዮን ዶላር ገቢ ውስጥ መክፈል የነበረበትን 2.5 ሚልዮን ዶላር ታክስ ባለመክፈሉ እ.ኤ.አ በ2007 በዓቃቤ ሕግ ክስ ተመስርቶበት ፍርድ ቤት ቀርቧል።

ማርክ አንቶኒ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሲያስረዳ፤ ቢዝነሱን የሚከታተል የፋይናንስ ማናጅመንት እንደቀጠረና ምን ያህል ግብር መክፈል እንደነበረበት አለማወቁን ተናግሯል። ዓቃቤ ሕግም አንቶኒ ያቀረበውን ሃሳብ ተቀብሎ መክፈል የነበረበትን 2.5 ሚሊየን ዶላር እንዲከፍል ወስኗል። የቢዝነሱ ማናጀሮች ግን ወንድሙ ቢግራም ዛያስን ጨምሮ ሆን ብለው ወይም በግድየለሽነት አንቶኒ ታክስ እንዲከፍል ባለማድረጋቸው ፍርድ ቤቱ በእስራት እንዲቀጡ ወስኗል።

**ማርታ ስቲዋርት፡-** ማርታ ሔለን ስቲዋርት በአሜሪካ አሉ ከሚባሉ ስመ-ጥር የንግድ ሰዎች አንዷ ስትሆን የተሳካላት ጸሐፊም ናት። ማርታ "Omni media" የተሰኘ የሚዲያ ተቋም መስራችም ናት። እናም፤ ከነዚህ ተግባሮቿ ያገኘችው በርካታ ገንዘብ ባለቤት ሆናለች።

የአሜሪካ የደህንነትና የገንዘብ ምንዛሬ ኮሚሽን ባደረገው ማጣራት ከአጠቃላይ ገቢዋ ለመንግሥት መክፈል ከነበረባት 45ሺ 763 የአሜሪካን ዶላር 4ሺ 835ቱን እንደሸሸገች ጠቁሟል።

የማያስጥል ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# የንግድ ሥርዓታችን ፈተና የሆነው የመርካቶ አየር በአየር ሽያጭ

**በሺመልስ ሲሳይ**



ከሃገራችን ግብይት አብዛኛው በመርካቶ እንደሚካሄድ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ምክንያቱም፤ ግብይቱን የሚያከናውኑት ከመላ ኢትዮጲያ የመጡ ነጋዴዎች ናቸውና! በዚህ አካባቢ ማንኛውም ግብይት በደረሰኝ ብቻ መከናወን ቢኖርበትም በተግባር ላይ ያለው በተቃራኒ ነው።

ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ከ10 ዓመታት በፊት ባካሄደው ጥናት በመርካቶ ከሚካሄደው ግብይት ውስጥ 75 በመቶው ለመንግሥት ገቢ እንደማይሆን አረጋግጧል። ይህ የሚያሳየው በአብዛኛው ግብይት ያለደረሰኝ መከናወኑን ነው።

ለዚህ ችግር መከሰት በርካታ ምክንያቶች ቢጠቀሱም ያለደረሰኝ ግብይት አንዱ መሆኑ በጥናቱ ላይ ተመልክቷል።በተመሳሳይ ይሄው ችግር አሁንም በሥፍራው እየተስተዋለ እንደሚገኝ ማረጋገጥ ተችሏል። ለዚህ ችግር መከሰት ሦስት ምክንያቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የመጀመሪያው ምክንያት፤ በሀገሪቱ የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈጥሩት ችግር ነው።አብዛኛው በማምረቻው ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ድርጅቶች የትኛውንም ሽያጭ ሲያከናውኑ ደረሰኝ የመስጠት ልምድ ቢኖራቸውም ጥቂት የማምረቻ ድርጅቶች ይህንን አሠራር ተግባራዊ አለማድረጋቸው ነው።ይህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባደረገው የኢንተለጀንስ ሥራ ተረጋግጧል።

የንግድ ሥርዓታችን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ገቢን ለማሳደግ ቅንጅታዊ አሠራር በትግራይ

**በሰለሞን ወርቁ**

በትግራይ ክልል የሚገኙ የገቢው ዘርፍ አካላት ገቢን ለማሳደግ በቅንጅት እየሠሩ እንደሚገኙ ባደረግነው ቅኝት መረዳት ችለናል።ገቢ ሰብሳቢ አካላቱ የመቀሌ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ የመቀሌ ከተማ ገቢዎች ቢሮ እና የትግራይ ክልል ገቢዎች ቢሮ ሲሆኑ ተግባራቸውን በቅንጅትም ሆነ በተናጠል ሲያከናውኑ ነበር።

‹‹የመቀሌ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከዋናው መሥሪያ ቤት ስልጠና ማዕከል ጋር በመቀናጀት ለሁሉም ሠራተኞች እንዲሁም ለክልል እና ለከተማው ገቢዎች ቢሮ ባለሙያዎች በሥነ-ልቦና፣ በሰው ኃይል እና በታክስ ሕጎች ላይ ስልጠና እንዲሰጥ አድርጓል። ከሚያዝያ 2015 ዓ. ም ጀምሮ ደግሞ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራዎችን በሲስተም መሥራት ጀምሯል።

ከዚህ ሌላ ለግብር ከፋዮች የሞጁላር ስልጠናዎች እየተሰጠ ሲሆን የፌደራል ግብር ከፋዮች አብዛኛዎቹ የሂሳብ መዝገብ የሚጠቀሙ እና የሚያደርጉት የግብይት ልውውጥም በደረሰኝ ብቻ የሚያደርጉ ናቸው። በዚህ በኩል ከክልል ገቢዎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መድረኮች ተፈጥረው አሁንም የግንዛቤ ማስጨበጫዎች በክልሉ የቴሌቪዥን ጣቢያ ለማስተላለፍ የበጀት እጥረቱ እስኪስተካከል እየተጠበቀ ነው።

በዋናነት የንግድ ስርዓቱ መስመር መያዝ ስላለበት ከመቀሌ ከተማ ገቢዎች ቢሮ እና ከክልሉ ገቢዎች ቢሮ ጋር በመግባባት እና በመናበብ እየሠራን ነው።



አቶ ተክላይ አብርሃ
የመቀሌ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ

በትግራይ ክልል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀጽ



## ስጋራ ጥቅም በጋራ እንታገል!

በቅርቡ ተከብሮ በነበረው ዓለም አቀፍ የጸረ-ሙስና በዓል ላይ የሰማነው አንድ መረጃ በጸረ-ሙስና ትግሉ ላይ ሁሉም ቢተባበር የሀገርን ኢኮኖሚ በቁሙ እየበላ ያለውን ሙሰኝነት በእጅጉ በቀነሰው ነበር።

በቅርቡ በ75 የዓለም አገራት በተደረገ ጥናት፤ ለ156ሺ ሰዎች መሞት፣ ለዘጠኝ ሚሊዮን ህዝብ መጠለያ አልባ መሆን እና ለ584ሺ ሰዎች ለጉዳት መዳረግ ምክንያቶቹ ህንጻዎች ሲገነቡ በሙሰኛ ኮንትራክተሮች፣ የግንባታ ተቆጣጣሪዎች እና የመንግስት ሠራተኞች መካከል በሚደረግ የጥቅም ግንኙነት ነው።የጥቅም ግንኙነቱ የሚዘጋጀውን የኮንክሪት ውህድ ከደረጃ በታች በማድረግ እና ተገቢውን የግንባታ ብረት ባለመጠቀም የሕንጻ መደርመስ ይከተላል።

የአፍሪካ የኢኮኖሚ ልማት የ2020 ሪፖርት ደግሞ፤ አፍሪካ 88.6 ቢሊዮን ዶላር ወይም ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርቷ (ጂዲፒዋ) ሦስት በመቶ ገንዘቧ በአንድ ዓመት ውስጥ በሙስና ምክንያት ይመዘበራል።

በ2022 የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የሙስና ቅኝት ጥናት ሪፖርት መሠረት 38 በመቶ የሙስና ስጋት የተመዘገበባት ሀገራችን በዚህ ይዘቷ ከ180 ሀገራት 94ኛ ላይ ተቀምጣለች።አደጋውን ለመቀነስ በቅርቡ በተሠራ ሙስናን የመከላከል ተግባር ከዘጠኝ ቢሊየን ብር እና ከአራት ሚሊየን ካሬ ሜትር በላይ መሬት ከምዝበራ ማዳን ተችሏል።ይህ የሆነው የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማካሔድ የሁሉም ተሳትፎ ስለታየበት ነው።

በዚህ ረገድ አንድ የጉምሩክ አስተላላፊ «ጉዳያችሁን በጉምሩኮች አስፈጽምላችኋለሁ» ብሎ ጉቦ ሊቀበል ሲል የጠቆሙ ባለጉዳይ መልካም ምሳሌ ናቸው።

የጉምሩክ አስተላላፊው፤ ለኢንቨስትመንት ዓላማ ከቀረጥ ነጻ የገባን ቶዮታ ሀይሉክስ ተሽከርካሪ ለአንድ ባለጉዳይ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለመፈፀም ተስማምቶ ነበር።በዚህም መሠረት የመኪናውን የሰባት ዓመት ቀረጥ እና ታክስ አንድ ሚሊየን 511ሺ 356 ብር ከ66 ሣንቲም እንዲከፍሉና ተሽከርካሪውን በአካል እንዲያቀርቡ ተናግሯቸዋል።

ግለሰቡ ቃሊቲ ጉምሩክ ሲቀርቡ በተከሳሹ የተነገራቸው፤ ተሽከርካሪው ለጥያቄ ስለሚፈለግ ጉምሩክ ዋና መሥሪያ ቤት መቅረብ እንደሚገባቸው ነው። ይህ እንዳይሆን እና ተሽከርካሪው እንዲለቀቅ ከፈለጉ ከጉምሩክ ኮሚሽን ኃላፊዎች ጋር እንደሚያደራድራቸው አግባብቶ መኪናውን ለመልቀቅ አንድ ሚሊየን ብር ጉቦ እንዲከፍሉ ጠይቋቸዋል።እርሳቸውም የተስማሙ በመምሰል ለሕግ ሰዎች በማሳወቃቸው በተካሔደው ክትትል በባንክ የተዘጋጀውን የአንድ ሚሊየን ብር ቼክ ሊቀበል ሲል እጅ ከፍንጅ ተይዟል።

ይህ የሚያሳየው፤ ሙስናን ማስወገድ እና እና ወደሙስና የሚወስዱ መንገዶችን መዝጋት የሚቻለው በኅብረተ-ሰቡ ተሳትፎ ጭምር መሆን ነው።ስለዚህ፤ በምንም መንገድ ከሕግ አሠራር ውጪ የሚመጣን የእጅ መንሻ ጥያቄ እና ሕጋዊ መንገድን ያልተከተለ አካሔድ ባለመቀበል አገልግሎት የማግኘት መብትን አስከብሮ ከፀረ-ሙስና ትግሉ ጎን መቆም ተገቢ ነው።ከዚህ አኳያ ግብር ከፋዮቻችንም አንዱ የዚህ ተግባር ተከላካዮቻችን ናችሁና ማንኛውንም አገልግሎት በሕጋዊ መንገድ ከማስፈጸም አልፎ ከመስመር የሚወጡ ሲያጋጥሟችሁ በመጠቀም ሕጋዊነት እንዲሰፍን ድርሻችሁን ልታበረክቱ ይገባል።ይህ ሲሆን የራስም፣ የሕዝብም ሆነ የመንግሥት ጥቅም ይከበራል።

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ
የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ አካሉ ጴጥሮስ ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
ሰሎሞን ወርቁ

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 11-6-17-84-90 ኮድ 8490 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

**ስታክስ እና ስጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199**

# የማያስጥል ዝነኝነት

ከገጽ 1 የዞረ



በዚህም ምክንያት ብዙ ክሶች ተመስርቶባት ኒውዮርክ ፍርድ ቤት ቀረበች።

የክሱ ዝርዝር ቀርቦ ምርመራ ከተደረገባት በኋላ የአምስት ወር እስር እና የሁለት ዓመት የቁም እስረኛ እንድትሆን ተወስኖባታል። ከዚህ በተጨማሪ ለአምስት ወር ከማንኛውም የመምረጥ እና የመመረጥ መብቷ እንድትታገድ የተደረገች ሲሆን 30ሺ የአሜሪካ ዶላርም ቅጣት ጥሎባታል።




**ዊስሊ ስናይፕስ፡-** አሜሪካዊው ተዋናይ ዊስል ትሬንት ስናይፐስ የፊልም አዘጋጅ እና የአክሽን ፊልሞች ድንቅ ተዋናይ ነው። አብዛኞቻችን የፊልም ተመልካቾች ይህንን ተዋናይ የምናውቀው ሦስት ተከታታይ ክፍሎች ባሉት “Blade” በተሰኘ አክሽን ፊልሙ ነው።

ዊስሊ የ12 ዓመት ታዳጊ ሳለ የጀመረው የማርሻል አርት ስፖርት በኋላ ላይ ለሠራቸው የአክሽን ፊልሞች ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተውለታል። ይህ ሰው በሾተካን ካራቴ የ“5ኛ ዳን” እና በሐብኪዶ የ“2ኛ ዳን” ጥቁር ቀበቶ ባለቤት ነው።

ይህ የሆሊውድ ኮከብ እ.ኤ.አ. ከ1986-2015 የሠራቸው ፊልሞች 48 ሲሆኑ በቴሌቭዥን የተላለፉ ተከታታይ ድራማዎች ደግሞ 11 ናቸው። በእነዚህ ሥራዎቹ እስከተጠቀሰው ዘመን ድረስ 15 የተለያዩ ሽልማቶች ባለቤት ሲሆን ከዚያ በኋላም በርካታ ፊልሞች እና ድራማዎች ላይ ሠርቶ የተለያዩ ሽልማቶችን ተቀብሏል።

በአሜሪካ የደረሰው የሰፕቴምበር 11ዱ የሽብር ጥቃት የበርካታ አሜሪካውያንን ሕይወት ከመቅጠፉም በላይ በብዙ ቢሊየን ዶላር የሚገመት ንብረቷን ማውደሙ ይታወሳል። በዚህ ጥፋት የዊስሊ ስናይፐስ የንግድ ቤት ከነንብረቱ ሁለት የንግድ ማዕከል ህንጻዎች ሲወድሙ ሙሉ በሙሉ ወድሟል።

እ.ኤ.አ. በ1997 54ኛው የቬነስ ፊልም ፌስቲቫል በተዘጋጀበት ወቅት ዊስሊ ስናይፐስ፣ “one night stand” በተሰኘው ፊልሙ ባሳየው ድንቅ ብቃት በምርጥ ተዋናይነት ዘርፍ አሸንፏል። ከዚህም በተጨማሪ በቀጣይ ዓመት ትልቅ የገበያ ስኬትን በማስመዝገብ ከተለያዩ የፊልም ሥራዎቹ ከ150 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ አግኝቷል።

ነገር ግን ይህ ሰው ከሚያገኘው ገቢ ተገቢውን ታክስ ለመንግሥት መክፈል ይገባው የነበረውን 17 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ባለመክፈሉ የአሜሪካ የታክስ ሰብሳቢ ተቋም ጉዳዩን ፍ/ቤት አድርሶታል። ፍ/ቤቱም ባደረገው ማጣራት ያለበትን ዕዳ ከነወለዱ እንዲከፍል እና በፈፀመው ሕገ-ወጥ ድርጊት በሦስት ዓመት እስር



**ዊሊ ኔልስን፡-** አሜሪካዊው ዊሊ ኔልስን ሙዚቀኛ፣ ደራሲ፣ ጸሐፊ፣ ገጣሚ እና ንቁ የፖለቲካ ሰው ነው። ዊሊ፤ የመጀመሪያውን የዘፈን ግጥሙን የጻፈው ገና የሰባት ዓመት ታዳጊ ሳለ ነበር። አስር ዓመት ሲሞላው ከሙዚቃ ባንድ ጋር ሆኖ መሥራት ቢቀጥልም ድንገት የሙዚቃ ሥራውን አቋርጦ ትምህርት ቤት በመግባት እስከ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቀቀ። ትምህርቱን እንደጨረሰም የአሜሪካ የአየር ኃይልን ቢቀላቀልም ጀርባው ላይ ባጋጠመው ህመም ተሰናብቶ ባይሎር ዩኒቨርሲቲ በመግባት የከፍተኛ ትምህርቱን አጠናቀቀ። ሆኖም ከልጅነቱ ጀምሮ ውስጡ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# እንግዶቻችን

አዘጋጅ:- ሺመልስ ሲሳይ

# ለዘመኑ የግብር አሰባሰብ

የገቢዎች ሚኒስቴር ለግብር ከፋዮች ይበልጥ ተደራሽ ለመሆን እየተጠቀመባቸው ካሉ የቴክኖሎጂ ስርዓቶች ውስጥ አንዱ የተቀናጀ የመንግሥት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (Standard Integrated Government Tax Administration System - SIGTAS) ነው። ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎት አሰጣጡን ይበልጥ ዘመናዊ፣ ተገልጋይ ተኮር፣ የታክስ ሕግ ተገዢነት ወጪን የሚቀንስና ተደራሽ ለማድረግ ዘመኑ የደረሰባቸውን የቴክኖሎጂ አማራጮች መዘርጋት ይጠበቅበታል።

ለዚሁም ይህንን ሥርዓት በተቀናጀ ታክስ አስተዳደር ስርዓት (Integrated Tax Administration System - ITAS) ለመቀየር እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፕሮግራም አስተዳደር ጽ/ቤት የለውጥና ተግባቦት ሥራዎችና ድጋፍ ኤክስፐርት ከሆኑት ከአቶ ብሩክ ኪዳኔ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**የተቀናጀ የመንግሥት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት ሥራ የጀመረው መቼ ነው?**

ይህ ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1996 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደርን በመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓት ለማስተናገድ ነበር ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገው። በ1999 ዓ.ም. ሌሎችንም የግብር ዓይነቶች እንዲያካትት ተደርጎ እስካሁን ድረስ ይሄው ሥርዓት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ሆኖም ግን ይህ ሥርዓት ግብር ከፋይ ተኮር እና ዘመናዊ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም የማዘጋጃ ቤታዊ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑ በታሰበው ልክ ለግብር ከፋዮች ተደራሽ እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ላይ ውስንነቶች ይስተዋሉበታል።

**ይህንን ሥርዓት ወደተቀናጀ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት መቀየሩ ያስፈለገበት ዋንኛ ምክንያት ምንድን ነው?**

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለግብር ከፋዩ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን መጠቀም ያስፈልጋል።

የተቀናጀ የመንግሥት ታክስ አስተዳደር ስርዓት በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችን እየፈታ ቢገኝም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በርካታ የአሠራር ሥርዓቶች ታክለውበታል። የታከሉበት አገልግሎቶችም ኤሌክትሮኒክ ማስታወቅ፣ ኤሌክትሮኒክ ክፍያ፣ ቴሌ ብር ወዘተ ናቸው። የነዚህ አገልግሎቶች በዚህ ሥርዓት ላይ መካተት በአንድ ጊዜ በርካታ ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት (Concurrent Session) እያጨናነቀው መጥቷል። በዚህም የተነሳ ለግብር ከፋዮች ፈጣን አገልግሎት መስጠት አልተቻለም።

ከዚህም በተጓዳኝ በዓለም ባንክ የቀረበው የመረጃ ቴክኖሎጂ የትንትና (የዲያግኖስቲክ) ጥናት፤ የተቀናጀ የመንግሥት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) የአገልግሎት ዘመኑን ማራዘም ተገቢ አለመሆኑን አስቀምጧል። ይህ ሥርዓት በተሻለ ቴክኖሎጂ መቀየር እንዳለበት ምክረ-ሃሳብ በመቅረቡ ሌላይኛው ምክንያት ነው።

**የለውጡን ሂደት ለማስኬድ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ምንድን ናቸው?**

የመጀመሪያው ተግባር የመረጃ ቴክኖሎጂ ዲያግኖስቲክ ጥናት ማካሄድ ነው። ይህም ፕሮጀክቱን በሚደግፈው በዓለም ባንክ ተካሂዷል። በመቀጠልም የተካሄደውን ጥናት በሚኒስቴር መ/ቤት ደረጃ ማጽደቀ ነው። በቀጣይም ይህ ፕሮጀክት በኢንፎሮሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (በኢንሳ) በኩል እንዲለማ ስምምነት ላይ ተደርሶ ቴክኖሎጂው በመልማት ላይ ይገኛል። የገቢዎች ሚኒስቴርም ሥራውን በመከታተል ላይ ይገኛል።

**ይህ ፕሮጀክት ተጠናቆ ሥራ ሲጀምር ምን ምን አገልግሎቶችን ይሰጣል?**

ፕሮጀክቱ ተጠናቆ አገልግሎት ሲጀምር ሁሉን አቀፍ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት፣ የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ዕዳ አስተዳደር፣ የኤሌክትሮኒክስ የቅሬታ አስተዳደር፣ የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት፣ የኤሌክትሮኒክስ የደረሰኝ ልውውጥ፣ ግብር ከፋዮች ወደ ገቢ ሰብሳቢ ቅርንጫፎች መሄድ ሳያስፈልጋቸው ባሉበት ቦታ ሆነው የግብር ከፋይ ምዝገባ፣ ማሳወቅ፣ ክፍያና ከታክስ ዕዳ ነጻ ማስረጃ (Tax Clearance service) አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ መስጠት ያስችላል።

**ፕሮጀክቱን እውን ለማድረግ ከማን ምን ይጠበቃል?**

ዓለም አንድ መንደር ከሆነች ሰንበትበት ብላለች። በዚህ ተለዋዋጭ ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ የሚቻለው የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን መጠቀም ሲቻል ነው። የገቢዎች ሚኒስቴርም እነዚህን የቴክኖሎጂ አማራጮች ለተገልጋዮች ለማቅረብና አሠራሩን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ወረቀት አልባ ለማድረግ በሂደት ላይ ይገኛል።

በመሆኑም ግብር ከፋዮች ይህንን የቴክኖሎጂ አማራጭ በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ መንግሥታዊ ባለበጀትና የልማት ድርጅቶች ከግዢና ሽያጫቸው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በቀጥታ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ አዲሱ ሥርዓት ጋር ማያያዝ ይኖርባቸዋል። ይህም ወረቀት አልባ በሆነ መንገድ የመረጃ ልውውጥ ዘዴን ለመፍጠር ተቋማቱ በቴክኖሎጂዎች እርስ በእርስ እንዲገናኙ ያግዛል። ስለሆነም እነዚህ ተቋማት ለዚህ ቴክኖሎጂ ተግባራዊነት የራሳቸውን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል።

ሥርዓቱ በአግባቡ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ለተገልጋዮች እንዲሰጥ መብራት ኃይልና ኢትዮ ቴሌኮም የኃይል እና የኔትወርክ አገልግሎትን ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ መልኩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በማቅረብ የተለመደ ትብብራቸውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።



በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፕሮግራም አስተዳደር ጽቤት የለውጥና ተግባቦት ሥራዎችና ድጋፍ ኤክስፐርት አቶ ብሩክ ኪዳኔ፤



አይታስን ከማስተዋወቅ ጀምሮ ከተካሔዱት ውይይቶ የአንዱ መድረክ ተሳታፊዎች፤

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- ለሰሞን ወርቁ

## ደንበኞች ሊያሟሉ የሚገባቸው ጉዳዮች

ካለፈው የቀጠለ

**ሀ. የክፍያ ጊዜ ስምምነት/ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት አገልግሎት አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የግብር/ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ፤
- ውሉን የሚፈራረመው ሥራ አስኪያጅ ከሆነ ማንነትን የሚገልፅ ማስረጃ እና የንግድ ፈቃድ ኮፒ፤ ተወካይ ከሆነ ሕጋዊ ውክልና እና መታወቂያ ኮፒ፤
- በአቤቱታ/ክርክር ላይ የነበረ ከሆነ ክርክሩን እያየው ከነበረ አካል ክርክሩን በራስ ፈቃድ ስለማቋረጡ ማስረጃ፤
- የዕዳውን 25% ቅድሚያ ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ ማቅረብ፤
- የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ የቀረበው ሃብት/ንብረት ከተያዘ በኋላ ከሆነ የታክስ ባለስልጣኑ ጉዳዩን ለማስፈጸም ያወጣችውን ወጪዎች እና ቢያንስ የታክስ ዕዳውን 25% ቅድሚያ ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ ማቅረብ፤
- ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ከሆነ የታክስ ባለስልጣኑ የታክስ ዕዳ አሰባሰቡን ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ እንደ አግባብነቱ እና ቢያንስ የታክስ ዕዳውን 25% ቅድሚያ ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ ማቅረብ፤
- በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ የተለየ፣ ሃብት በዕዳ የተያዘበት ወይም ንብረት እንዲሸጥ ጨረታ የወጣበት ታክስ ከፋይ ዕዳውን ለመክፈል የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ቢያንስ የታክስ ዕዳውን 25% ቅድሚያ ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ እና ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ማቅረብ አለበት።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት/ቡድን

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ለ. የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት**

አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- የክፍያ ጊዜ ተሰጥቶት ግዴታውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻለበትን ማስረጃ ማቅረብ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሐ. መቀጫ ይነሳልኝ አገልግሎት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የመቀጫ ይነሳልኝ ማመልከቻ ማቅረብ፤
- የሚፈለግባቸውን ፍሬ ግብር ወለድ እና የማይነሳውን መቀጫ የከፈለበትን ደረሰኝ ማቅረብ፤
- ማንነትን የሚገልፅ ማስረጃ ተወካይ ከሆነ ህጋዊ ውክልና እና መታወቂያ ኮፒ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**መ. በታክስ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት መልቀቅ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የንብረቱ ባለቤት ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ተወካይ ከሆነ ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ እና የመታወቂያ ኮፒ ማቅረብ፤
- የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት ለንብረቱ መያዝ ወይም መከበር ምክንያት የሆነው የግብር ዕዳ እንዲሁም ንብረቱን ለመያዝና ለማስከበር የወጣው ወጪ በሙሉ የተከፈለበትን ሰነድ ማቅረብ፤
- የግብር ዕዳው የተሰረዘ ወይም በምህረት እንዲቀር የተደረገ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ፤
- እዳውን በክፍያ ስምምነት መሰረት ለመክፈል ስምምነት የገባ ታክስ ከፋይ ከሆነ በውሉ መሰረት ቀሪ ክፍያውን ሙሉ በሙሉ የከፈለበት ማስረጃ ወይም ከቀሪ ክፍያው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ማስረጃ ማቅረብ፤
- የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት በህግ የማይከበር ወይም የማይያዝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ፤
- የግብር ባለ ዕዳ ግብር ባለመክፈል ምክንያት የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የያዘው ወይም ያስከበረው ንብረት ይገባናል የሚሉ 3ኛ ወገኖች ንብረት ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ማቅረብ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሠ የተሸጠ ንብረት ለገዢ ለማስረከብ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ጨረታ ያሸነፈበት ደብዳቤ፤
- መታወቂያ/ውክልና ማስረጃ፤
- ገዢ የጨረታ አሸናፊነቱ በደብዳቤ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ገንዘብ የከፈለበትን ማስረጃ ማቅረብ፤
- በጨረታ ሽያጭ ንብረት የገዛ ሰው ገንዘቡን ገቢ ባደረገ ከ10 እስከ 20 የሥራ ቀናት ውስጥ ንብረቱን ለማንሳት ጥያቄ ማቅረብ፤
- በርክክቡ ዕለት እና ቦታ ተገኝቶ መረከብ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ረ. ግብር እና ታክስ ውሳኔ ላይ ለሚቀርብ ቅሬታና አቤቱታ አገልግሎት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 54/1/ በተደነገገው መሰረት በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ቅሬታ አቅራቢ የታክስ ውሳኔ በጽሑፍ በተሰጠው በ21 /ሃያ አንድ/ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለክፍሉ ማቅረብ፤
- ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔውን የሚቃወምበት ምክንያቶች፣ ታክስ ከፋዩ ውሳኔውን ለማስተካከል ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎች እና እነዚህን ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት በቅሬታ ማመልከቻው በትክክል መግለጽ እና ማቅረብ፤
- ቅሬታውን ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ መሰረት መከፈል ያለበትን እና በቅሬታ ማስታወቂያው ተቃውሞ ያላቀረበበትን ታክስ የከፈለ እና ስለመክፈሉም ማስረጃ ማቅረብ፤
- የቅሬታ ማቅረቢያው ጊዜ ካለፈ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ማቅረብ የሚችለው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው በደረሰው በ21 /ሃያ አንድ/ ቀናት ውስጥ ወይም የሚሰጠው ማስታወቂያ በደረሰው በ10 /በአስር/ ቀናት የቅሬታ ማስታወቂያውን በጽሑፍ ማቅረብ፤
- ቅሬታ አቅራቢው በጊዜ ገደቡ ውስጥ ቅሬታ ማቅረብ ካልቻለ ማቅረብ ያልተቻለው በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ ወይም በህመም ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት በማቅረብ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ከማለፉ በፊት ታክስ ከፋዩ በታክስ ውሳኔ ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ የማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት ለከፈለው በጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ፤
- በተሰጠው የአቤቱታ ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ያለው ታክስ ከፋይ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 88/1/ መሰረት የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ የጸደቀውን ቅጅ በመጠቀም በውሳኔው ላይ የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረብና ይህንኑ ታክስ ለሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት ማሳወቅ፤
- ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አቤቱታ የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ በክርክር ላይ ያለውን ታክስ (ቅጣትና ክፍያ የዘገየበት ወለድ ሳይጨምር) 50 በመቶ መክፈል።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤቶች ደጋፊና ክትትል ጽ/ቤት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሰ. የቴምብር ስርጭትና ሽያጭ አገልግሎት**

**1) ስርጭት ከሆነ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- በሚመለከተዉ ኃላፊ ተፈርሞ የቀረበ የጥያቄ ደብዳቤ፤
- ክፍያ መፈፀም፤
- ከዚህ በፊት ለተሰራጨ የአጠቃቀም ሪፖርት፤
- የዉክልና ደብዳቤና መታወቂያ ኮፒ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የገቢ ሂሣቦች አስተዳደር ዲይሬክቶሬት
- የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**2) ሽያጭ ከሆነ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ሰነድን ማቅረብ፣
- ክፍያ መፈፀም፣

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር የሥራ ሂደት/ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሸ. የግብር እፎይታ አገልግሎት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ፣ፓስፖርት፤
- ውክልና ከሆነ የውክልና ህጋዊ ማስረጃ፤
- የግብር እፎይታ የተፈቀደበት ደብዳቤ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
- የታክስ ማስታወቅ የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ቀ. የሪከርድና ማህደር አገልግሎት**

**ወጪ ደብዳቤ መስጠት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ፣ፓስፖርት ውክልና ከሆነ የውክልና ህጋዊ ማስረጃ፤
- ኦሪጂናል ደብዳቤ መውሰዱን የሚያረጋግጥ ፊርማ መፈረም።

**ገቢ ደብዳቤ መቀበል**

- ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ፣ፓስፖርት ውክልና ከሆነ የውክልና ህጋዊ ማስረጃ፤
- የመስሪያ ቤት ከሆነ የመ/ቤቱ ህጋዊ ደብዳቤ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- ሪከርድና ማህደር አገልግሎት
- ሪከርድና ማህደር ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**በ. ለጠቋሚ የወሮታ አበል ክፍያ አገልግሎት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ኦሪጅናል የጠቋሚ ድርሻ፤
- ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ማቅረብ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ማጭበርበር ምርመራ ዲይሬክቶሬት እና የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት
- የታክስ ማጭበርበር ምርመራ ቡድን /የግዥና ፋይናንስ ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ተ. ለተያዘበት ንብረት ማስረጃ የመስጠት**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የተያዘው ዕቃ፣ ተሽከርካሪ ወይም ማሽነሪ ከሆነ ባለንብረቱ ተሽከርካሪው ወይም ማሽነሪው የተሟላ መሆኑን ማሳየት፤
- የተሽከርካሪው ወይም የማሽነሪው ቁልፍ እና ሊብሬ ማስረከብ፤
- ዕቃው ተቆጥሮ መረካከቢያ ሰነድ ላይ መፈረም።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ማጭበርበር ምርመራ ዲይሬክቶሬት እና የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት
- የታክስ ማጭበርበር ምርመራ ቡድን /የግዥና ፋይናንስ ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ቸ. የተያዘ ንብረት (ዕቃ) የመልቀቅ**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ተሽከርካሪው እንዲለቀቅለት ማመልከቻ፤
- በፍርድ ቤት የተወሰነ ከሆነ የፍርድ ቤት ውሳኔ፤
- የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ከሆነ የከፈለ ስለመሆኑ ደረሰኝ (ሰነድ)።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ማጭበርበር ምርመራ ዳይሬክቶሬት እና የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት
- የታክስ ማጭበርበር ምርመራ ቡድን /የግዥና ፋይናንስ ቡድን

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

# በየዓይነቱ

## አስሩ የፔሌ ልዩ መታወቂያዎች









መላው ዓለም በእግር ኳስ ንጉሥነቱ የሚስማማበት ኤዲሰን አራንቴስ ዶ ናሲሜንቶስ፤ በአጭር አጠራር ፔሌ፤ ሦስት የዓለም ዋንጫዎች በማንሳት በታሪክ ብቸኛው ከመሆኑ በተጨማሪ በርካታ ግቦችንም በማስቆጠር የክብረ ወሰን ባለቤት ነው።

ባለፈው ዓመት በ82 ዓመቱ ያረፈው ፔሌ፤ የእግር ኳስ ነገር ሲነሳ ስሙ በቀዳሚነት የሚጠቀስ እና ታሪኩ ላለፉት ስድሳ ዓመታት በመላው ዓለም ሲነገር ቆይቷል። የፔሌ አብዛኛዎቹ ታሪኮች እና ገጠመኞቹ በስፋት ቢነገሩም ብዙም ያልተባለለቸው አስር ጉዳዮች ግን አሉት።

### 1ኛ. ለፔሌ ሲባል ዳኛ ከሜዳ ተባርሯል፤

እ.ኤ.አ. በ1968 የብራዚል ቡድን ለኦሊምፒክ ውድድር ዝግጅት የወዳጅነት ጨዋታ ለማድረግ ከኮሎምቢያ አቻው ጋር ቦጎታ ውስጥ ገጥሞ ነበር። በወቅቱ ቀይ ካርድ ሥራ ላይ ውሎ ስላልነበረ የጨዋታው ዳኛ ጉሌርሞ ቬላስኬዝ፤ ፔሌ በኮሎምቢያ ተጫዋች ላይ ጥፋት በመፈጸሙ ከሜዳ እንዲወጣ አዘዙ። በዚህ ጊዜ በስታዲየሙ ውስጥ ብጥብጥ ተፈጠረ።

ብራዚላውያኑ ተጫዋቾች የቡድናቸው ወሳኝ ተጫዋች ከሜዳ እንዲወጣ መታዘዙ አስቆጣቸው፣ የእግር ኳሱን ኮከብ ለመመልከት ስታዲየም የታደሙት ኮሎምቢያውያንም የፔሌን ከሜዳ መባረር በመቃወማቸው ግርግር ተፈጠረ። ዳኛውም በተፈጠረው ውዝግብ መሃል ጉሽማ ደርሶባቸው ፊሽካቸውን ለአንደኛው የመስመር ዳኛ አስረክበው ከሜዳ ሲወጡ ፔሌ ወደ ጨዋታው እንዲመለስ ተደርጎ ግጥሚያው ቀጥሏል።

### 2ኛ. የፔሌን ጨዋታ ለማየት ተኩስ አቁም ተደርጎ ነበር፤

በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1960ዎቹ ፔሌ የሚጫወትበት የሳንቶስ ቡድን በዓለም ላይ ካሉ ዝነኛ ክለቦች መካከል አንዱ በመሆኑ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኙ የወዳጅነት ጨዋታዎችን በዓለም ዙሪያ እየተጓዘ ያደርግ ነበር።

ከእነዚህ ጨዋታዎች መካከል ሳንቶስ በ1969 በእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ወደነበረችው ናይጄሪያ በመሄድ በቤኒን ከተማ ካለ ቡድን ጋር ተጋጥመው የፔሌ ቡድን 2ለ1 አሸንፏል።

በወቅቱ ቢያፍራ የተባለችውን ግዛት ከናይጄሪያ ለመገንጠል የተጀመረ ጦርነት ይካሄድ ነበር። ፔሌ የሚገኝበት የሳንቶስ ቡድን የደኅንነት ስጋት ስለነበረው ለጨዋታ ከማምራቱ በፊት ተዋጊዎቹ ወገኖች ተኩስ ለማቆም ተስማምተው ነበር።

በእርስ በርስ ጦርነቱ የሚሳተፉት ወገኖች ጨዋታው በሚካሄድበት ወቅት ጦርነቱን እንደሚያቆሙ እና አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ጥቃት እንደማይሰነዝሩ አረጋግጠዋል። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ዝነኛው ፔሌ በቡድኑ ውስጥ በመካተቱ ነው።

### 3ኛ. ታዋቂዎቹ "ዘ ቢትልስ' ፔሌን እንዳያዩ ተከልክለዋል፤

ፔሌ ፕሮፌሽናል ተጫዋች ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1975 አሜሪካ በመሄድ ኒውዮርክ ኮስሞስ የተባለን ቡድን ተቀላቅሎ ነበር። ከቡድኑ አባላት ጋር ለመግባባት እንዲያግዘው ኒውዮርክ ከደረሰ በኋላ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት መማር በጀመረበት ጊዜ በዘመኑ በሙዚቃው ዘርፍ በመላው ዓለም ተወዳጅ የነበሩት የ'ዘ ቢትልስ' የሙዚቃ ቡድን አባል ከሆነው ከጆን ሌነን ጋር ተገናኝተዋል።

በ1966 እንግሊዝ ውስጥ የዓለም ዋንጫ ሲካሔድ ታዋቂዎቹ ሙዚቀኞች ፔሌን እና የብራዚል ብሔራዊ ቡድን ተጫወቾችን ለማየት ሞክረው ነበር። ነገር ግን ሌነን ለፔሌ እንደነገረው የዘ ቢትልስ ሙዚቀኞች ሙከራ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። ይህም የሆነው በወግ አጥባቂ የብራዚል እግር ኳስ ማኅበር ባለሥልጣናት እምቢተኝነት መሆኑን ፔሌ ጽፏል።

### 4ኛ. ፔሌ ለአውሮፓ ቡድን አልተጫወተም

የፔሌ ተቺዎች፤ ፔሌ እግር ኳስን በአውሮፓ ክለቦች ውስጥ ተጫውቶ አለማወቁ «ያለተቀናቃኝ ‹የእግር ኳስ ንጉሥ› እየተባለ ለመዝለቅ ሕይወቱን ቀላል አድርጎለታል» ይላሉ። ለዚህ ግን ችግሩ የፔሌ አልነበረም። እንደሚነገረው ከሌሎች ብራዚላውያን ተጫዋቾች በተለየ ፔሌ ዝነኛ በነበረባቸው ዓመታት ወደ ውጪ አገር ሄዶ እንዳይጫወት ታግዶ ስለነበር ነው።

በወቅቱ በተጫዋቾች ዕጣ ፈንታ ላይ ክለቦች ወሳኝ ስለነበሩ ክለቡ ሳንቶስ ከሪያል ማድሪድ እና ከኤሲ ሚላን ፔሌን ለመውሰድ የቀረበለትን ጥያቄ ሳይቀበለው ቀርቷል። ፔሌ ብራዚል ውስጥ ብቻ እንዲጫወት ግፊቱ ከመንግሥት በኩልም መጥቶ ነበር። በ1961 የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ጃኒዮ ኳድሮስ፣ ፔሌ "ወደ ውጪ ሊላክ የማይችል ብሔራዊ ሀብት ነው" ብለው አወጀው ነበር።

ነገር ግን ከዓመታት በኋላ ፔሌ የአሜሪካውን ኒው ዮርክ ኮስሞስ ቡድንን በመቀላቀል በውጪ አገር ቡድን ውስጥ ተሰልፎ የመጫወት ዕድል አገኘ።

### 5ኛ. ፔሌ የቡድኑ አምበል ሆኖ አያውቅም

ምንም ያህል የእግር ኳስ ጥበበኛ ቢሆን እና ዝናው በዓለም ቢናኝም ፔሌ በእግር ኳስ ዘመኑ በአምበልነት በጨዋታ ላይ የተሳተፈው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ለአገሩ ብሔራዊ ቡድንም ሆነ ለቡድኑ አምበል እንዲሆን ሲጠየቅ ፈቃደኛ ስላልሆነ ነው።

ፔሌ ለአንድ ጊዜም ቢሆን የአምበልነቱን መለያ ክንዱ ላይ ያሰረው ከብሔራዊ ቡድኑ ተሳትፎ ራሱን ካገለለ ወይም ጫማውን ከሰቀለ ከ19 ዓመታት በኋላ በ1990 ለፔሌ 50ኛ ዓመት በተዘጋጀው ጨዋታ ላይ ነው።

ጨዋታው ጣሊያን ሚላን ውስጥ የተካሄደ ሲሆን በብራዚል ብሔራዊ ቡድን እና ከመላው ዓለም የተወጣጡ ታዋቂ ተጫዋቾች መካከል ሲሆን ፔሌ በመጀመሪያው 45 ደቂቃ ተሰልፎ ተጫውቷል።

### 6ኛ. ፔሌ ከሜዳ «ተጠልፎ» ተወስዷል፤

የሳንቶስ ቡድን ተጫዋቾች በ1972 ለግጥሚያ ወደ ካሪቢያኗ አገር ትሪንዳድ ኤንድ ቶቤጎ ለግጥሚያ በሄዱበት ጊዜ በአገሪቱ ሰላም ስላልነበረ በቶሎ ግጥሚያቸውን አደርገው ወደ አገራቸው ለመመለስ ጓጉተው ነበር።

ነገር ግን በጨዋታው ላይ በ43ኛው ደቂቃ ፔሌ ግብ ሲያስቆጥር ያልጠበቁት ነገር ተከሰተ። በስታዲየሙ የነበሩት ተመልካቾች በደስታ ሜዳውን ጥሰው ገቡ። ከዚያም ግብ ያስቆጠረውን ፔሌን በትከሻቸው ላይ ተሸክመው ከስታዲየም ውጪ ይዘውት በመውጣት በጎዳናዎች ላይ እየጨፈሩ ደስታቸውን ይገልጹ ነበር።

በወቅቱ ከቡድኑ አባላት ተለይቶ በደጋፊዎቹ ወደ ጎዳና የተወሰደውን ፔሌን ከትከሻቸው ላይ አውርዶ ከቡድኑ ጋር ለመቀላቀል ከፍ ያለ ጥረትን ፈልጎ ነበር።

### 7ኛ. በፊልም ላይ የራምቦን ቦታ ፔሌ ተክቶ ነበር

በ1980 'ኢስኬፕ ቱ ቪክትሪ' የተባለው ፊልም ሲቀረጽ ሲልቭስተር ስታሎን (ራምቦ) በፊልሙ ዓለም ዝነኛ ተዋናይ ነበር። 'ኢስኬፕ ቱ ቪክትሪ' የተሰኘው ልቦለዳዊ ፊልም በናዚ ቡድን እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት እስረኛ በነበሩ ተጫዋቾች መካከል የሚደረግ የእግር ኳስ ግጥሚያ ታሪክን የሚያሳይ ነው።

በዚህ ፊልም ላይ ታዋቂዎቹ እግር ኳስ ተጫዋቾች ፔሌ፣ ቦቢ ሙር እና ኦሲ አርዲልስ የተሳተፉበት ሲሆን ሲልቭስተር ስታሎን ደግሞ በረኛ ሆኖ ተሰልፏል። በፊልሙ ላይ ፔሌ በመቀስ ምት ኳስ ሲመታ የሚታይበት አንድ ክፍል አለ። ይህ ክፍል ሲቀረጽ በመጀመሪያው ሙከራ ፔሌ በድንቅ ሁኔታ የሚፈለገውን የመቀስ ምት ሲመታ ተቀርጿል።

ፔሌ እንደተናገረው ይህን የፊልም ክፍል መጀመሪያ ላይ ሲልቭስተር ስታሎን እንዲተውነው ነበር የታቀደው። ነገር ግን እሱ ያንን ማድረግ ባለመቻሉ ፔሌ ያቺን የመቀስ ምት ግብ ሲያስቆጥር እንዲቀረጽ ተደረገ።

### 8ኛ. ፔሌ በረኛ ሆኖ ሲጫወት ግብ አልተቆጠረበትም፤

ፔሌ የሚታወቀው በአጥቂነት ቦታ ባለው ድንቅ ችሎታ እና ሚና በመሆኑ የተዋጣለት ግብ ጠባቂ ስለመሆኑ ብዙም አይነገርም። ለዚህም ቡድኑ አንድ ተጫዋች ብቻ የመቀየር ግዴታ ሲኖርበት ፔሌ የበረኛውን ቦታ በመረከብ ወሳኝ ተጫዋች ወደ ሜዳ እንዲገባ ያደርጋል።

በተጨማሪም ለሳንቶስ ቡድን በተጫወተባቸው ዓመታት አራት ጊዜ በረኛ ሆኖ የተሰለፈ ሲሆን አንደኛው ቡድኑ ለብራዚል ሻምፒዮና ለግማሽ ፍጻሜ በደረሰበት ወቅት ነበር። ፔሌ በግብ ጠባቂነት በተሰለፈባቸው በነዚህ ጨዋታዎች ላይ አንድም ግብ ተቆጥሮበት አያውቅም።

### 9ኛ. በፔሌ ስም የሚታወቁ በርካታ ታዋቂ ተጫዋቾች፤

ከዝነኛው ፔሌ በኋላ በርካታ በእርሱ ስም የሚጠሩ ሰዎች በመላው ዓለም ተፈጥረዋል። እነዚህም በእግር ኳስ ሜዳ እና በሌለው መስክ የሚታወቁ ናቸው። በተለይ ድንቅ የእግር ኳስ ችሎታ ላላቸው ታዳጊዎች «ፔሌ» የሚለውን ቅጽል ስም መስጠት የተለመደ ሲሆን በስሙ ከመጠቀም አልፎ ድንቅ የእግር ኳስ ችሎታቸውን አስመስክረዋል።

ከእነዚህም መካከል በአፍሪካ ዝነኛ እግር ኳስ ተጫዋች የነበረው ጋናዊው አቤዲ አዩው፤ በአፍሪካ እና በአውሮፓ ክለቦች ውስጥ ሲጫወት በስፋት የሚታወቀው «አቤዲ ፔሌ» በሚለው ስሙ ነው።

የኬፕ ቬርዲው ተከላካይ እና በ2006 ለእንግሊዙ ሳውዝ ሃምፕተን የተጫወተው ፔድሮ ሞንቴሮ፤ በልጅነቱ በወጣለት «ፔሌ» በተሰኘው ቅጽል ስሙ ይታወቅ ነበር።

የእግር ኳሱ ንጉሥ የስም ተጽእኖ ፔሌ በሚለው ስሙ ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ኤዲሰን አራንቴስ ዶ ናሲሜንቶስ ከሚለው ስሙ ላይ የመጀመሪያውን በመውሰድ ብዙዎች ለልጆቻቸው ሰጥተዋል።

ፔሌ ዝነኛ ከሆነ በኋላ በብራዚል ውስጥ ኤዲሰን የሚለው ስምም በብዙዎች ዘንድ ተመራጭ መሆኑን የአገሪቱ ስታትስቲክስ ተቋም ገልጿል። በ1950ዎቹ በአገሪቱ ውስጥ ኤዲሰን በሚለው ስም የሚጠሩ 43ሺ 511 ሰዎች ነበሩ። ከ20 ዓመታት በኋላ ፔሌ አንድ ሺ ጎሎችን ሲያስቆጥር እና በሦስት የዓለም ዋንጫዎች አሸናፊ ሲሆን የስሙ ተፈላጊነት ጨምሮ ኤዲሰን የሚባሉት ሰዎች ቁጥር ወደ 111ሺ ደርሶ ነበር።

### 10ኛ. የብራዚል ፕሬዝዳንት የመሆን ፍላጎት ነበረው፤

በ1990 ፔሌ ከአራት ዓመታት በኋላ በሚካሄደው የብራዚል ፕሬዝዳንትንት ምርጫ ላይ እንደሚወዳደር ለዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን አሳውቆ ነበር። ነገር ግን እንዳለው ለመሪነት ዕጩ ሆኖ ባይቀርብም ወደ ፖለቲካው ዓለም በመግባት መሳተፍ ጀመረ። በዚህም መሠረት ከ1995 እስከ 1998 የብራዚል ስፖርት ሚኒስትር ሆኖ አገልግሏል።

በዚያ ወቅትም እሱን በውጭ አገራት ቡድኖች ውስጥ ተሰልፎ እንዳይጫወት ያደረገው የቡድኖች ጫና እንዲቀንስና ተጫዋቾች በወደፊት ዕጣቸው ላይ ለመወሰን የሚያስችል ሕግ እንዲወጣ ጥረት አድርጓል።

## የማያስጥል ዝነኝነት

ከገጽ 2 የዞረ

የነበረው የሙዚቃ ፍቅር ዳግም ወደ ሙዚቃው እንዲመለስ አስገደደው።

ዊሊ የሙዚቃ ሕይወቱን የተመለሰበት በቴክሳስ ሬዲዮ ጣቢያ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ1956 ወደ ዋሽግተን በማቅናት "Family Bible" የተሰኘ ሙዚቃ ሠርቷል። በ1958 ደግሞ ወደ ሒውስተን በመጓዝ ሙዚቃውን ከፍ ባለ ደረጃ መሥራት የሚያስችለውን አጋጣሚ ከታዋቂው የሙዚቃ አሳታሚ "D Records" ጋር ተፈራረመ።

የሙዚቃው ደረጃ እያደገ የመጣው ዊሊ ኔልሰን እ.ኤ.አ. በ1973 ከአትላንቲክ ሪከርድስ ጋር አዲስ ኮንትራት በመፈራረም በወቅቱ አሜሪካ የሚገኙ የማፊያ ቡድኖችን የሚቃወሙ "Shot gun willie» እና «phases and stages» የተሰኙ አሳተመ።

ነገር ግን ከነዚህ ስኬቶቹ ጀርባ መክፈል ነበረበትን ታክስ ባለመክፈሉ ክስ ተመስርቶበታል። እ.ኤ.አ. በ1990 የአሜሪካ የገቢ ሰብሳቢ ተቋም በዊሊ ኔልሰን ላይ ባደረገው ማጣራት ለመግሥት መክፈል የነበረበትን 16 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር እንዳልከፈለ በምርመራ ተረጋገጠ። በዚህም የተነሳ በባንክ አካውንቱ ላይ የተገኘው 32 ሚሊየን ዶላር እንዳይንቀሳቀስ ታገደበት።

በመቀጠል ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሲታይ ከቆየ በኋላ መክፈል ይጠበቅበት የነበረውን 16 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ከነወለዱ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን አስተላልፎበታል።



**ኒኮላስ ኬጅ፡-** ኒኮላስ ኬጅ የሥነ-ጽሑፍ ፕሮፌሰር፣ ዳንሰኛ እና ኬሮግራፈር ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በትያትር ት/ቤት ውስጥ ስለፊልም እና ስለቴሌቪዥን ተምሯል። ለመጀመሪያ ጊዜ ከሲኒማ ውጪ በተወነው ተውኔት ላይም «ወርቃማው ልጅ» እስከመባል ደርሷል።

ሆሊውድ ውስጥ ትልቅ ተከፋይ የነበረው ኒኮላስ ኬጅ እ.ኤ.አ. በ2009 ብቻ 40 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ገቢ አግኝቷል። ነገር ግን ከ6.2 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር በላይ የገቢ ግብር ባለመክፈሉ በሐምሌ 2009 የአሜሪካ የገቢዎች አገልግሎት ዶክመንቶቹን እና አዲስ ግንኙነቶችን በሙሉ በግብር ዕዳ እንዲያዙ አደረገበት። በተጨማሪም እ.ኤ.አ. ከ2002 እስከ 2004 350ሺ ዶላር በላይ በወለድ አግድ ይዞበታል።

ኬጅ፤ ጥቅምት 16/2009 ባደረገው ከፍተኛ ሙግት 20 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ወደ ወኪል የቢዝነስ ማናጀሩ እንዲገባ አድርጓል። እንደ ቀድሞው ማናጀሩ ገለፃ ዝቅተኛ በሆነ እና አደጋ ባለው ሪልስቴት መጀመሩ እና ታክስን በአግባቡ መክፈል ባለመቻሉ የአሜሪካ የአገር ውስጥ አገልግሎት እቃ እንዳያወጣ እገዳ ጥሎበታል። ነገር ግን እስካሁን ይከፍላል በሚል እምነትና ተስፋ ለእስር አልዳረገውም።

# የንግድ ሥርዓታችን ፈተና የሆነው ...

ከገጽ 1 የዞረ

ሁለተኛው ምክንያት፤ በአስመጪዎች በኩል የሚታይ ችግር ነው።መንግሥት የዜጎችን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ በመመደብ በሃገር ውስጥ የማይመረቱ ምርቶች ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።ነገር ግን እነዚህ አስመጪዎች ይህንን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ተመድቦለት ወደ ሃገር ውስጥ የገባው ምርት በህጋዊ መልኩ በደረሰኝ መሸጥ ሲኖርባቸው አየር በአየር ሲሸጡ ይስተዋላል።

ሦስተኛው ምክንያት፤ የኮንትሮባንድ ምርት በከፍተኛ ደረጃ ወደ መርካቶ መግባቱ ነው።እነዚህ ምርቶች ወደ ሃገር ውስጥ ሲገቡ በሕገ-ወጥ መንገድ መሆኑ ይታወቃል።ሃገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ግብይታቸው የሚፈጸመው ደግሞ ያለደረሰኝ መሆኑ ለችግሩ መከሰት መንስኤ ነው።

ዘርፉን እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው የገቢዎች ሚኒስቴርም ያለደረሰኝ ግብይት በሃገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።ከነዚህም መካከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት አንዱ ነው።ይህንንም ለማከናወን የኦፕሬሽን ቡድን አዋቅሮ ቡድኑን በመምራት ግንባር ቀደም ሚናውን በመጫወት ላይ ይገኛል።ቡድኑም ከገቢዎች ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ከኦሮሚያ ክልል የተውጣጣ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮም ባለፉት አምስት ወራት የችግሩን አሳሳቢነት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።ከተግባራቱ መካከል በንግድ ድርጅቶች ላይ የተካሄደው ጥናት ተጠቃሽ ነው።የጥናቱ ዓላማም ደረሰኝ በማይቆርጡ እና ሀሰተኛ ደረሰኞችን ተጠቅመው የግብይት ሂደቱን በማስተጓጓል የራሳቸውን ጥቅም ያስቀደሙ አካላትን ለመለየት ነው።ጥናቱ በ800 የንግድ ድርጅቶች ላይ የተካሄደ ሲሆን ከድርጅቶቹ ወስጥ ከ400 በላዮቹ ላይ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

ከዚህም በተጓዳኝ ቢሮው ባላፉት አምስት ወራት ብቻ ባካሄደው የኦፕሬሽን ተግባር ምንም ዓይነት ግብይት ሳይፈጸም ሃሰተኛ ደረሰኝን በመጠቀም ብቻ የ26 ቢሊዮን ብር ግብይት እንደተፈጸመ በማስመሰል ሃሰተኛ የገንዘብ ዝውውር ያከናወኑ የድርጅት ባለቤቶችን በቁጥጥር ስር አውሏል።

ያለደረሰኝ ግብይት የሃገርን ብሄራዊ ጥቅም በከፍተኛ ደረጃ ከሚጎዱ ተግባራት ውስጥ በዋናነት ተጠቃሽ ነው።ይህንን ሕገ-ወጥ ድርጊት መከላከል የመንግሥት ተልዕኮ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የንግድ ማህበረሰብ ብሎም ሸማች የትኛውንም ግብይት ሲፈጽም ደረሰኝ የመጠየቅ ልምድ ሊኖረው ይገባል።

አምራቾች፣ አስመጪዎች እና አከፋፋዮችም የትኛውንም ሽያጭ ሲያከናውኑ ደረሰኝ መስጠት ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል።የሃገራችን የፍትህ ሥርዓትም በታክስ ጉዳዮች ላይ አበረታች ተግባራትን እያከናወነ ቢሆንም ከዚህ በበለጠ ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅበታል።

# ገቢን ለማሳደግ ቅንጅታዊ...

ከገጽ 1 የዞረ

**የመቀሌ ከተማ ገቢዎች ቢሮ**

‹‹የገቢዎች ሚኒስቴር ለከተማው ገቢዎች ቢሮ ሠራተኞች የሥነ-ልቦና እና ማህበራዊ ግንኙነት /psycho-social/ ስልጠናዎችን ለሦስት ዙር በመስጠቱ ለሥራችን አጋዥ ነውና ይቀጥል። ከስልጠናው በኋላ ግብር ከፋዮች በፊት ወደነበሩበት የግብር አከፋፈል ሥርዓት ለመመለስ እየሠሩ ነው። ከዚህ ሌላ የተሻለ አፈጻጸም ካስመዘገቡት አዋሳ፣ አዳማ እና አዲስ አበባ ከተሞች ገቢዎች ልምድ እንድንወስድ ቢመቻችልን የበለጠ ጥሩ ይሆናል።

ከግብር ከፋዮቻችን 870ዎቹ ወደ ፌደራል ግብር ከፋይነት የተሸጋገሩ ቢሆኑም በቀጣይ የተሻለ የግብር አሰባሰብ እንዲኖር በደረሰኝ አሰጣጥ እና ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከገቢዎች ሚኒስቴር መቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር በጋራ እየሠራን ነው።

የንግድ ሥርዓቱ ገና ሥርዓት እንዳይኖረው ካደረገው መካከል የመርካቶ ጉዳይ ነው። ግብር ከፋዮች አዲስ አበባ በመሔድ እቃዎችን ከሚገዙበት ከመርካቶ ደረሰኝ ስለማይሰጣቸው ወይም ደረሰኝ በሚቆረጥባቸው ደግሞ ሻጮቹ ዋጋ አሳንሰው ስለሚቆርጡ ነጋዴዎቻችን ተቸግረዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ከሁሉም ነጋዴዎች ጋር ውይይት ያደረግን ቢሆንም አሁንም ችግሩ አልተቀረፈም።

ሌላው፤ በከተማው ውስጥ ያሉ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ድርጅቶች የደረሰኝ አሠራር ላይ ከመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር በጋራ እየሠራን ነው። በዚህ በኩል የተፈለገውን ያህል ውጤት ባይገኝም በደረሰኝ አሰጣጥ ላይ የተሻሉት ሆቴሎች ናቸው››



**አቶ ሰሎሞን ትኩእ**
**የመቀሌ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ**

**የትግራይ ክልል ገቢዎች ቢሮ**

‹‹የፌደራል ተሞክሮን በመውሰድ በመቀሌ ዙሪያ የተጀመረ ዓመታዊ ሽያጫቸው 10 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ የሆናቸውን ግብር ከፋዮች በመለየት ለብቻቸው አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው። የደረሰኝ ቁጥጥር ሥርዓትም ሥርዓት እንዲኖረው በትኩረት እየተሠራበት ነው።

በሌላ በኩል፤ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር እያካሔድን ባለው የመረጃ ልውውጥ በሕግ ማስከበር የተለያዩ ክትትሎችን ማድረግ ጀምረናል። በክትትሉም ሕገ-ወጥ ደረሰኝ አሳትመው የሚሠሩ ሰዎችን አግኝተን እጅ ከፍንጅ ይዘናል። እንዲሁም፤ ያለደረሰኝ ግብይትም ስለሚፈጸም ይህንን ሥርዓት የማስያዝ፤ በድርጊቱ ፈጻሚዎችም ላይ እርምጃ የመውሰድ ሥራ ተጀምሯል። እንዲሁም ሕጋዊ ደረሰኞችን የማረጋገጥ ሥራ እየሠራን ነው። በተለይ ምንም ግብይት ሳይፈጸምባቸው በደረሰኝ መልክ ብቻ ገበያ ላይ የዋሉ ደረሰኞችን መዝግበን በማጣራት ወደ እርምጃ እየገባን ነው።

በክልላችን ደረሰኝ አሳትመው ‹ደረሰን ጠፍቶብናል› በማለት ወደ ሦስተኛ ወገን በሕገ-ወጥ መንገድ ለማስተላለፍ የሚሞክሩትን ለመከላከል በጋራ እየሠራን ነው። ዋናው የማጭበርበሪያ ስልቱ ሕገ-ወጥ ደረሰኝ ነው። በዚህ ማጭበርበር ተሰማርተው ያገኘናቸው ሁለት ድርጅቶች ናቸው።

የፌደራል ተሞክሮን በመውሰድ በመቀሌ ዙሪያ የጀመርነው ዓመታዊ ሽያጫቸው ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑትን 350 ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ለይተናቸዋል። እነዚህ ግብር ከፋዮችም ብቻቸውን አገልግሎት የሚያገኙበት አሠራር ለመጀመር ባለሙያዎችን መድበን የዕቃ አመዘጋገብ እና ስርጭት ላይ እየተሠራ ነው።እንዲሁም፤ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የደረሰኝ ጉዳይ ላይ የግንዛቤ ሥራ እየተሠራ ነው።



**አቶ ተስፋዬ ታደሰ**
**የትግራይ ክልል ገቢዎች ቢሮ የሕግ ማስከበር ዳይሬክተር**

# Regarding...

Continued from page 7

3. Late payment penalty paid by a taxpayer by article 50 (40 of this proclamation to the extent t hat the tax to which the penalty relates is found not to have been pageable
4. This article shall not apply when article 106 of this proclamation applies to the unpaid tax.

**Value Added Tax Penalties**

1. A person who fails to apply for registration as required under the Value Added Tax Proclamation shall be liable for a penalty of Birr 2,000 (Two Thousand Birr) for each month or part thereof for the period commencing on the date that the person was required to apply for registration and ending on the date that the person files the application for registration or the person is registered on the Authority's motion.
2. In addition to the penalty imposed under sub-article (1) of this article shall also be liable for a penalty of 100% of the amount of value-added tax payable on taxable transactions made by the person during the period commencing on the day on which the person was required to apply for registration and ending on the date the person applies for registration or the person is registered Authority's motion.
3. The imposition of penalty under sub-article (2) of this Article shall not relieve the person from the liability for the value added tax payable on tax payable on the taxable transactions made by the person during the period specified in that sub-article, but the amount of the value added tax payable is reduced by any turnover tax by the person on those transactions.
4. A person who deliberately issues an incorrect tax invoice resulting in a decrease in the value-added tax payable on a taxable transaction or an increase in the creditable value-added tax in respect of a taxable transaction shall be liable for a penalty of birr 50,000 (Fifty Thousand Birr).

**Tax understatement penalty**

1. A taxpayer whose declared tax liability is less than the taxpayer's correct tax liability (the difference being referred to as the "tax shortfall") shall be liable for a penalty of 10% of the tax shortfall
2. The penalty under sub-article (1) of this article shall be increased to 30% for the second application of the Article to the taxpayer.
3. The penalty under sub-article (1) of this article shall be increased to 40% for the third or subsequent application of the Article to the taxpayer.

No penalty shall be imposed under this Article if the tax shortfall arose as a result of a self-assessment taxpayer.



# Tips

BY SHIMELIS SISAY

## "If you don't honor your dreams, you will be kicked out!"

**BY ANILEY TIAHUN**






We have experienced change in the womb; We have changed. All progress is change, but not all change is progress. There are many occasions when a strong life can be an example of sacrifice.

Any kind of result we desire is a process. And the process is the way. on the way to "Success" the destination seems to be endless. But success is always what we live for, it is not something that we will reach or lose tomorrow. Because success is always inside us, not what we want or give us from outside. It is what you live from the moment you decide on your journey; Success, I believe, is the source of unceasing effectiveness and boundless happiness.

What is given to us from outside is a blessing or a gift, not a success, if a gift is for the work we're doing, we can see the cause as a stop on our journey as a reward for our inner self.

Success is an inexhaustible thorn (desire) is a lasting reward. It is raw energy that comes out from within. Trust me, if your thorn is beyond your ability, you will do well. Because most human abilities are acquired through education or practice. That's why it is said; "Seek and you shall find; knock and it shall be opened to you." So, wait for your desire. Quench your curiosity. See a clear picture in your imagination. Understand your path. Everything will come true. Just look at the path in your mind. Search the cellar of your mind; Examine it; The balance of your freedom and your life goal; Your pillar of safety; For it is one and two.

lucid or visible dream We can call it the frame of life. When you think about it, longing for success without realizing where you are going is like trying to touch the sky with your fingers?...

Man is a creature that is developing with skills and maturing with knowledge. Social chains are the reason for the creation of different systems. Check them out. Let your action be timely. Success is the result of smooth interaction with time. Understanding the contexts created by time and responding appropriately rewards one's potential. It will also be a standard, and I think this is why Ermiyas Amelga said; "If it doesn't fight me and test me, it's not my standard!"

Therefore, success is not just an aspiration; For the one who wants and baptizes his heart with mastery, who loves the context, who plans the method of getting it and finally follows up and executes what he planned, the "faith world" will embrace the million. This starts with identifying what you are doing. "There is no bread without work" When a person achieves what he wants to achieve, we call it success. Therefore, life is like a restaurant. We get what we want as long as we can pay for it. The main issue is our position on "how much should I pay after we understand our goal?"

Success is internal; A process that grows within us and guides our lives in the direction it wants. I can change; It is a self-deception that you can do. When we came to earth (when we left our mother's womb), we cried; And when we leave the earth, it should not be with regret and sorrow. This situation will be corrected by success. Therefore, when we live on earth, let us take what we deserve, live as we deserve, and serve the earth and the world that we have served in a wide way. We need to earn more than we used and serve the next generation... we need to get rid of regrets and pass on peacefully. It is not for this reason that the poet Kebede Michael remains;

"Whether or not there is righteousness condemnation;

Kindness is better than evil."

(The major key to your better future is you!)

Success means taking life seriously. It also means deciding one's destiny. When we say that we can determine our success by ourselves, we use human graces. Among these graces, imagination, and reason play the biggest role. So, these graces are the source of freedom. what is freedom? If it is said, "Being more competitive" means that each person strives to deliver the wisdom that is inside him in a way that can survive for himself and others. I think the saying "Great people create themselves" is more descriptive.

Your desire is a reflection of your inner truth. The source of your mastery lies in placing your identity in the proper context. This mastery is your invisible helper. It is the key to your life. Hold it. Therefore, have a hidden helper. The first step to success is finding an invisible helper; It is not an exaggeration to say that everything that is seen comes from something that is not seen. Therefore, shape your dreams. Believe in them. "He who has no faith, when the road is blocked, stops his journey." You are the driver of your dreams. Your stops; Your choices are yours. Your access is what you write.

## Regarding administrative penalties

Penalties relating to Registration and cancellation of registration

1. Subject to the other administrative penalties imposed by this proclamation, a person who fails to apply for registration as required under this proclamation shall be liable for a penalty of 25% of the tax payable by the person for the period commencing on the date that the person was required to apply for registration and ending on the date that the person files the application for registration or the person is registered on the Authority's motion.
2. Where there is no tax payable by the taxpayer mentioned in the sub-article (1) of this article, the taxpayer shall pay a penalty of Birr 1,000 (One Thousand Birr) for each month or part thereof from the day on which he should have been registered to the day of his actual registration.
3. Where the penalty to be imposed according to sub-article (1) of this article is less than the penalty to be imposed according to sub-article (2) of this article, the penalty in sub-article (2) of this article shall apply.
4. A person who, without reasonable excuse, fails to apply for cancellation of registration as required under this proclamation as required under this proclamation shall be liable for a penalty of birr 1,000 (One Thousand Birr) for each month or part thereof for the period commencing on the date that the person was required to apply for cancellation of the registration and ending on the date that the person files the application for cancellation or the person's registration is canceled on Authority's motion.

**Penalties concerning TINS**

1. A taxpayer who fails to state their TIN on a tax invoice tax debit or credit note, tax deceleration, or any other document as required under a tax law shall be liable for a penalty of birr 3,000 (Three Thousand Birr) for each failure.
2. Except when Article 14(6) of this proclamation applies, a taxpayer shall be liable for a penalty of birr 10,000 (Ten Thousand Birr) if the taxpayer;

a) Provides their TIN for use by another person: or

b) Uses the TIN of another person.

3. If the pecuniary advantage obtained by the taxpayer or another person as a result of conduct referred to in sub-article (2) (a) or (b)of this Article exceeds birr 10,000 (Ten Thousand Birr) the penalty shall be equal to the pecuniary advantage obtained by the taxpayer.

Late payment penalty

1. A taxpayer who fails to pay tax by the due date shall be liable for the following late payment penalties.

A) 5% of the unpaid that remains unpaid at the expiration of one month or part thereof after the due date: and

B) An additional 2% of the amount of the unpaid tax for each month or part of a month thereafter to the extent that the tax remains unpaid.

2. The amount of penalty assessed under this article shall not exceed the amount of the tax liability to which it relates.

Continued on page 6



ሕገ-ግብር

አዘጋጅ:- ሰሎሞን ወርቁ

# ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን ወንጀል

ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን ወንጀል የኢትዮጵያ የታክስ ሕግ ወንጀል አካል ሆኖ የተደነገገው በ2001 ዓ.ም. ሲሆን ይህም በአዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50 (ሐ) እና 50 (መ) 2 መሠረት ነው። ምንም እንኳን ጥቂት ለውጥ ቢደረግባቸውም እነዚህ አንቀፆች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 እና 131(1)(ለ) ላይ ከተደነገገውና ያለደረሰኝ ግብይትን የወንጀል ተግባር አድርጎ ከሚደነግጉት አንቀፆች ጋር የጎላ የይዘት ልዩነት የላቸውም።

## ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19/3 ላይ እንደተመለከተው ማንኛውም የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ለሚያከናውነው ግብይት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት ይላል ይህንን ሀሳብ የግብይት ምንነት እና የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ማነው የሚሉ ነጥቦች መለየት ያለባቸው ሲሆን በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 3 (1) እና (2) እና 82(1) እና (2) መሠረት ማንኛውም የደረጃ ሀ እና ለ ታክስ ከፋዮች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ተጥሎባቸዋል። በመሆኑም ማንኛውም ደረጃ ሀ እና ለ ታክስ ከፋዮች ግብይት በሚያከናውኑበት ወቅት የታክስ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ይኖርባቸዋል።

## ግብይት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 9/1/ ላይ እንደተመለከተው በመርህ ደረጃ የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ተከናወነ የሚባለው የዕቃ ርክክብ በተደረገበት ቦታ ነው። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 11/1 ላይ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ተከናወነ የሚባለው ለግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ በሚሰጥበት ወቅት መሆኑ ተመልክቷል። በአዋጅ ቁጥር 609/2008 አንቀጽ10/1/ ላይ እንደተመለከተው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያካሄድ ሰው ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት እንዳለበት ተመልክቷል።

አሁን ባለው የሕግ ማዕቀፍ የተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት የእቃ አቅርቦትና ደረሰኝ የመስጠት ተግባር አንድ ላይ መከናወን እንደለባቸው ሕግ ያስገድዳል። በመሆኑም ማንኛውም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያከናውን ታክስ ከፋይ ለሚያደርጋቸው ግብይቶች ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል። በመመሪያ ቁጥር 149/2011 ላይ እንደተመለከተው ገቢዎች ሚኒስቴር ታክስ ከፋዮችን እንዲጠቀሙት ብዙ አይነት ደረሰኞችን ሊፈቅድ ይችላል።

### እነዚህም:-

- የእጅ በእጅ የሽያጭ ደረሰኝ፤
- የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ፤
- የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ፤
- ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ፤
- የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ፤
- በገዥው ተይዞ ለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰጥ ደረሰኝ፤
- የታክስ ዴቢት ወይም የታክስ ክሬዲት ሰነድ፤
- የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ፤
- ቦን፤
- ትኬት
- የቫውቸር ደረሰኝ ሲሆኑ እነዚህ የማኑዋል ደረሰኝ በታክስ ባለስልጣኑ ዕውቅና ከተሰጠው ማተሚያ ቤት ታትመው ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

## ስደረሰኝ ግብይት የማከናወን ወንጀል

የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 131/1(ለ):- «ማንኛውም በሽያጭ መመዝገብያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፤ መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገብያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግይብት ካከናወነ፤ ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል» ይላል፡

ከላይ የተመለከተው መረዳት እንደሚቻለው ማንኛውም ሰው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በጥገና ላይ ከሆነ ወይም ሌሎች በቂ ምክንያቶች በመኖራቸው ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም ካልተቻለ በቀር ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጭ በሆነ በሌላ ማንኛውም ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን አይችልም። የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በሥራ ላይ እስካለ



| | | | |
|---|---|---|---|
| Invoice | 42 | Due Date | 08-Jul-2016 |
| Date Issued | 23-Jun-2016 | Address | 20 George St Sydney, NSW, 2000, Australia Edit |
| Currency | USD - United States Dollar | Subject | Design Public Website |
| Purchase Order # | | | |

Invoice Item Details

| Type | Description | Qty | Unit Price | Disc % | Tax Rate | Amount |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Content Acquisition | Homepage Design | 1 | 250,000.00 | 0 | No Tax | $ 250,000.00 |
| Laptop | Landing Page Design | 1 | 20,000.00 | 0 | Goods & Services Tax | $ 20,000.00 |
| Production | Film Production | 1 | 1,600.00 | 0 | No Tax | $ 1,600.00 |
| Expenses | [Game of Thrones Season 1 Episode 1] 04-Aug-2016 - David Benioff - (Travel) | 1 | 100.00 | 0 | No Tax | $ 100.00 |

| | |
|---|---|
| Total Discount | ($ 0.00) |
| Subtotal | $ 271,700.00 |
| + Tax of | $ 2,000.00 |
| Total Amount | $ 273,700.00 |
| Less Payment on 27-Jun-2016 (✖ delete) | ($ 60,000.00) |
| Amount Due | $ 213,700.00 |

ድረስ ታክስ ከፋዩ ግብይት ማከናወን ያለበት ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በሚወጣ ደረሰኝ ብቻ ነው። የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመያዝ ግዴታ ያለበት ማንኛውም ታክስ ከፋይ መሣሪያው በሥራ ላይ ባለበት ወቅት ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን ተግባር ወይም በሌሎች ደረሰኞች (ማኑዋል ደረሰኝን ጨምሮ) ግብይት ካከናወነ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክስ ይቀርብበታል።

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ዋነኛው ዓላማ ታክስ ከፋይ የሚያደርጋቸውን እያንዳንዱን ሽያጭ በአግባቡ መዝግቦ እንዲያቆይና ለገቢዎች ሚኒስቴር ሽያጩን በትክክል ሪፖርት እንዲደረግ ታስቦ ነው።

## በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን ስመመለስ ያስችል ዘንድ

በአንቀጽ 131/1/(ለ) የሚመለከተው ፍሬ ነገሮች ማየቱ አስፈላጊ ነው።

- የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን የመያዝ ግዴታ ያለበትን ታክስ ከፋይ ብቻ ነው። የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም የጀመሩ ሰዎች ማሽኑ ሥራ ላይ እያለ ሌሎች ደረሰኞች እንዳይጠቀሙ ያለመ ነው።
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በጥገና እና በሌሎች በቂ ምክንያቶች ሥራ ላይ ባልሆነበት ወቅት ፤ በማኑዋል ደረሰኝ የሚደረግ ግብይትም ሆነ በሌሎች ደረሰኞች የሚደረጉ ግብይቶች በዚህ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ አይደሉም። "የግብር ከፋዩ የታክሰ ማዕከል ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እስከፈቀደ እና ዕውቅና እስከሰጠ ድረስ።"

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በጥገና ላይ ነው ማለት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን ይችላል ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ወቅት ታክስ ከፋይ ግብይቱን የእጅ በእጅ ሽያጭ ደሰረኝ (ማኑዋል) በመጠቀም ግብይት የማከናወን ግዴታ አለበት። ሆኖም ማሽኑ በጥገና ላይ ሳለ ያለደረሰኝ ግብይት ተግባር የተከናወነ እንደሆነ ድርጊቱ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት የተፈፀመ በመሆኑ በታክስ አስተዳደር አዋጅ 131/1/(ለ) መሠረት የሚሸፈን ስላልሆነ የወንጀል ክስ ሊቀርብበት የሚገባው በአንቀጽ 120/1 መሠረት ነው።

በአንቀጽ 131/1/ለ/ ስር «ወይም» ከሚል ቃል በኋላ የተገለፀው «ያለደረሰኝ ግብይት» የሚል ሐረግ በአንቀጽ 131(1)(ለ) ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች በሌሉበት እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሥራ ላይ ባለበት የሚፈጸመውን ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን የወንጀል ተግባር ለማሳየት እንጂ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጥገና ላይ ባለበት ሁኔታ ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን ወንጀል የተከናወነ እንደሆነ የወንጀል ክስ የሚቀርበበትን ስርዓት የሚደነግግ አይደለም። ለዚህ ሀሳብ ግልፅነት የድንጋጌውን የእንግሊዝኛ ትርጉም ማየቱ አስፈላጊ ስለሆነ እንደሚከተለው ቀርቧል።

"If he, except at the time sale register machine is under repair, or other justifiable reason, carried out transactions without receipt or invoice or used any other receipt not generated by a sale register machine shall be punished with rigorous imprisonment 2-5"

ከላይ ከተመለከተው የእንግሊዝኛ ትርጉም ጭምር መረዳት እንደሚቻለው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ማሽኑ ጥገና ላይ ባለበት እና በሌሎች በቂ ምክንያቶች ሥራ ላይ ካልሆነ በቀር ማሽኑ ሥራ ላይ ባለበት ሁኔታ ያለደረኝ ግብይት የተከናወነ እንደሆነ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ውጭ በሚወጡ ወይም በሌሎች ደረሰኞች የሚደረግ ግብይት ሲኖር፤ ማለትም በማኑዋል፣ በኮምፒዩተር፣ በሀሰተኛ፣ በተፈቀዱ/ባልተፈቀዱ ደረሰኞች የሰጠ እንደሆነ በዚህ ድንጋጌ (131/1/ለ) መሠረት ክስ ሊቀርብ እንደሚገባ ተመልክቷል።

## የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሥራ ላይ በሌለበት ወቅት የሚፈፀም ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን ወንጀል

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ያልያዙ፣ ለመያዝ የማይገደዱ ነገር ግን የማንዋል ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች እና ማሽኑ ጥገና ላይ በመሆኑና በሌሎች በቂ ምክንያቶች አገልግሎት መስጠት በማይችልባቸው ጊዜያት ያለደረሰኝ ግብይት የተፈፀመ እንደሆነ የወንጀል ክስ ሊቀርብ የሚገባው በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 መሠረት ነው።

አንቀጽ 120/1:- "ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከብር 25ሺ እስከ 50ሺ የገንዘብ መቀጮ እና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል" ይላል። ይህ ከደረሰኝ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ደረሰኝ ሳይሰጥ ግብይት ካከናወነ የሚከሰስበትና የሚቀጣበት ድንጋጌ ነው።

ማንኛውም የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 መሠረት የወንጀል ክስ ይቀርብበታል፡ ይህ ድንጋጌ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚወጣውን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት ደረሰኝ የሚመለከት ነው። ሆኖም የአንቀጽ 120/1 እና 131/1(ለ) ተፈጻሚነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 አንፃር በአግባቡ መመርመር አለበት። ምንም እንኳን አንቀጽ 131 በዋናነት ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን የሚመለከት ቢሆንም የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ከደረሰኝ ጋር ተያይዞ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን የምንጠቀምበት አግባብ የሚደነግግ በመሆኑ ሁለቱ ድንጋጌዎች መቼና በምን ሁኔታ ተፈጻሚ እንደሚደረጉ መለየትና ከተደራራቢነት እና በአንቀጽ 61 ላይ ከተመለከተው ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት ከሚለው የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርሆ አንፃር በአግባቡ መመርመር ይኖርበታል። ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 አንፃር ሲታይ ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን ተግባር ተብሎ የቀረበው ድርጊት በአንድ ድንጋጌ ስር ሊሸፈን የሚችል፣ በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ የተፈፀመ እና ድርጊቱ ተመሳሳይ ሲሆን እንደሆነ በአንቀጽ 120/1 እና በ131/1/(ለ) መሠረት በአንድ ተግባር ላይ ሁለት የወንጀል ክስ የሚቀርብበት አግባብ አይኖርም።

## አንቀጽ 120/1 ተፈጻሚ የሚሆንበት አግባብ:-

- በ131/1(ለ) ላይ በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን ወንጀል ስር የማይሸፈኑ ተግባራት ተፈፅመው ሲገኙ፣

ለምሳሌ:- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጥገና ላይ እያለ ያለ ደረሰኝ (ያለ ማኑዋል ደረሰኝ) ባልተፈቀዱ ደሰረሰኞች ግብይት የተከናወነ እንደሆነ የወንጀል ክስ ሊቀርብ የሚገባው በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነው።

ያለደረሰኝ ግብይት ወንጀል ጉዳይ ላይ በተከሳሽ የሚቀርቡ መከላከያዎች

ያለደረሰኝ ግብይት ከመከናወን ወንጀል ክስ ጋር ተያይዞ በሙግት ሂደት በጠበቆችና ተከሳሾች በርካታ መከራከሪያዎች ይነሳሉ። ለምሳሌ:-

- ግብይቱ አልተጠናቀቀም፤
- ሥራ አስኪያጅ በወቅቱ በስፍራው አልነበረም፤
- ተገቢው የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል፤
- እኔ ሳላውቅ ውክልና ተሰጥቷል፤
- እኔ ሳልፈቅድ የተከናወነ ግብይት ነው፤
- ያለደረሰኝ ግብይት እንዳያከናውኑ ሠራተኞቼን አስፈርሚያለሁ፤
- «ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሂሳብ አይክፈሉ» የሚል ጽሑፍ በሚታይ ስፍራ ተለጥፏል፤
- ምስክሮች ወከባ ፈጥረውብኝ ነው አንጂ ደረሰኝ እቆርጥ ነበር፤
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያችን ተበላሽቶ ነበር፤
- የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ጥገና ላይ ነበር፤
- በወቅቱ መብራት ጠፍቶ ነበር፤
- የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ዕቃውን ከእኔ አልገዙም እና ሌሎች ምክንያቶች በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና በመከላከያነት ይቀርባሉ።

ከላይ የተመለከቱትን የክርክር ነጥቦች የሚያነሱት ግለሰብ ነጋዴዎችና የድርጅት ሥራ አስኪያጆች ሲሆኑ እያንዳንዱ መከራከሪያዎች በአግባቡ ሳይመረመሩ «ይህ መከላከያ ተገቢ ነው፤ ሌላኛው ተገቢ አይደለም» ለማለት አይቻልም። «ግብይት አልተጠናቀቀም» በሚል የሚነሳውን ክርክር ብንወስድ፤ ያለግብይት ስለደረሰኝ ማውራት አይቻልም። ግብይት ያልተጠናቀቀ ወይም የግብይቱ ባህሪ የተቀየረ እንደሆነ ታክስ ከፋይ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አይኖርበትም።

በተከሳሽ በኩል በብዛት የሚቀርበው መከላከያ «ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት ዘርግቻለሁ» የሚለው ሲሆን የዚህ መከራከሪያ መነሻ የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 132 ነው። በእርግጥ «ምን አይነት ተግባራት ሲከናወኑ ነው ተገቢ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል የሚባለው?» የሚለው ነጥብ አስማሚ አይደለም። በአንድ የሕግ ባለሙያ ተገቢ የአሠራር ሥርዓት የሆነ ተግባር ለሌላኛው ባለሙያ በቂ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ፤ ታክስ ከፋይ ውክልና የሰጠ በመሆኑ ብቻ ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት ዘርግቷል በሚል የሚከራከሩ ባለሙያዎች አሉ።

የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/2 ላይ እንደተመለከተው አንድ ድርጅት የወንጀል ተግባር መፈፀሙ በዐቃቤ ሕግ ተረጋግጦ እንደሆነ -

ሥራ አስኪያጅ ከወንጀል ነፃ የሚሆነው፤ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132 ላይ በተመለከተው--

- ወንጀሉ የተፈጸመው ሥራ አስኪያጁ ሳይፈቅድ ወይም ሳያውቅ ከሆነ እና
- በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያለና ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብለው የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ለማድረግ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ፤
- ውክልና በመስጠት ብቻ ሳይሆን ውክልና ከመስጠት በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132 ላይ በተመለከተው አግባብ ተገቢ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑና ለአስተዳደራዊ ሥራ የሚሰጥ ውክልና ተገቢ የሆነ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን የማያሳይ መሆኑን መግለጽ፤
- የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር 54061 እና በወንጀለኛ መቅጫ ቁጥር 48850 ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ነው።

**ምንጭ**:- Wondiye Birhanu (Taxation Blog)

የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

እ ሴ ቶ ች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)